
# ትንሣኤ

የበዐለ ሃምሳ አከባበር

የማተብ ማሰር ልማድ



የኢትዮጵያና የኤሮፓውያን
የገና በዐል ልዩነት

የዐርብና የረቡዕ
ጾም ዝርዝር ሁኔታ

የቅዳሜና የእሁድ
አከባበር የት–መጣ

፩ኛ፡ዓመት። — ቁጥር፡፲፡

www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም

በዚህ ለአራተኛ ጊዜ በወጣው « ትንሣኤ» መጽሔታችን ውስጥ በመጽሔቱ ጀርባ ሠፍረው የሚገኙትን አርእስተ ነገሮች የቃላቱን ፍቺ የት—መጣቸውን በታሪክ መልክ ፤ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያላቸውን ታዋቂነት ፤ ከሕዝብ ልማድ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ሊደረግ የሚገባውን መሻሻል በዝርዝር ፤ በጥልቅ ጥናት አቅርበናል ። ይህንንም ያደረግንበት ምክንያት ለምን እንደ ሚከበሩና ምን ዓይነት ታሪካዊ ጉዞ እንዳላቸው ለሕዝብ ለማስረዳት ስለአሰብን ነው

ስለዚህ ይህ መጽሔት በሕዝብ አእምሮ ዘንድ ሲጉላሉ የኖሩና እንዲሁም የሚኖሩ አያሌ ጥያቄዎችን እንደሚያብራራና ፤ ስለነዚህም አርእስተ ነገሮች በመጠኑ የሚፈለገውን ያህል ዕውቀት ሊያበረክት እንደሚችል እንተማመናለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ

አርእስት ፡                                                                 ገጽ


፩ኛ/ የኢትዮጵያና የኤሮፓውያን የገና በዓል ልዩነት . . . ፯

፪ኛ/ የበዓለ ሃምሳ አከባበር . . . . . . . . . . . ፲፯

፫ኛ/ የማተብ ማሠር ልማድ . . . . . . . . . . ፳፫

፬ኛ/ የዓርብና የረቡዕ ጾም ዝርዝር ሐተታ . . . . . ፳፯

፭ኛ/ የቅዳሜና የእሑድ አከባበር የትመጣ . . . . . . ፳፱




www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያና የኤሮፓውያን የገና በዐል ልዩነት

## ፩ ገና የቃል ፍች

፩ኛ/ ገና ማለት ከዕርዕ ቋንቋ የተወረሰ ሲሆን የቃሉ ትርጉም ልደት ማለት ነው ። እግዚአብሔር ለዓለም በሰጠው ተስፋ መሠረት የክርስቶስ መወለድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ፤ ይህም ዓለም የክርስቶስን የልደቱን በዓል ለማክበርና የደስታው ተካፋይ ለመሆን ተዘጋጅቶ የቀኑን መድረስ በታላቅ ናፍቆት ረዘም ላለ ጊዜ ሲጠባበቅ ቆየ ። ጊዜውም ሲደርስ በአውግስጦስ ቄሣር ዘመነ መንግሥት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም የሰጠውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም በቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም ተወለደ ። ጨለማና አሮጌ የነበረውም ዓለም አዲስ ዓለም ሆነ ፣ በዚህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ለአዲስ ዘመንና ለሥልጣኔ በር ታላቅ መክፈቻ ቁልፍ ሆኖ ተገኘ ።

በተጨማሪም በዓለም እስከ አሁን ድረስ ብዙ የደስታ ልውውጦች ቢደረጉም የክርስቶስ ልደት ግን ዘመን የማይሽረው ጊዜ የማይለውጠው አድናቆቱ የማይበርድበት አዲስ ለውጥ በመሆኑ በኃጢአት ታሥረው የነበሩ እስረኞች በነፃ ተፈቱ የሥጋና የመንፈስ ነፃነትም ለተቀበሉት ሁሉ ታወጀላቸው ።

ስለዚህ የክርስቶስ ልደት ለዓለም ሕይወት የተፈጸመ ራሱ አንድ ታላቅ ስጦታ ስለሆነ ቃል ሥጋን ለብሶ በዚህ ዓለም ሲሠራና ሲያስተምር በቆየበት ጊዜ ለእያንዳንዳችን የምንጠቀምበትን ምሳሌና ትምህርት ስለሰጠን ለሕይወታችን ዓይነተኛ መምሪያ ሆነልን ።

## ፪ኛ የትመጣው በታሪክ መልክ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን እርግጠኛውን ዕለት የአስትሮኖሚ የአርኬዎሎጂና የታሪክ ሊቃውንት ሲወያዩበት የቆየ አርዕስተ ጉዳይ ቢሆንም ወደ ፊትም እንዳከራከረ ይኖር ይሆናል ፤ ትክክለኛውን ዕለት የሚያረጋግጥ ታሪካዊ የጽሑፍ መረጃ እስካሁን ድረስ የተገኘ አይመስልም ። የክርስቲያን ቀን መቁጠሪያዎችም በዚህ ሁኔታ አይመሳሰሉም ፣ በጎርጎሪያን የዘመን አቆጣጠር የሚጠቀሙት የዓለም ሕዝቦች የክርስቶስን የልደት በዓል ኢትዮጵያውያን ከሚያከብሩት የልደት በዓል ፲፫ ቀን ቀደም ብለው ያከብራሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህስ እንዴት ሊሆን ቻለ ? አመጣጡስ እንዴት ነው ? የሚል ጥያቄ ይገጥመን ይሆናል ።

ክርስቲያኖች ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን ለመረዳት በጥብቅ ምርምር የጀመሩት በሦስተኛው መቶ ዓመት ይመስላል ፤ ቀሌምንጦስ የተባለው የእስክንድርያ ሊቅ ክርስቶስ የተወለደው ግንቦት ፳ ቀን ነው ሲል አስተያየቱን ሰጥቶ ነበር ። ቢሆንም የሮም ቤተ ክርስቲያን የጌታን ልደት በታኅሣሥ ፳፭ ቀን ታከብር እንደነበር ከ፫፻፴፮ ዓ. ም. ጀምሮ ግልጽ ነው ። ይህ ቀን በአሕዛብ ዘንድ የፀሐይ በዓል እየተባለ ይከበር ስለነበር ክርስቲያኖች ይህንን የጣዖት አምልኮ ጠባይ ያለበትን በዓል ለመቃወም ሲሉ የጌታን ልደት በዚሁ ቀን ማክበር ጀመሩ የሚል አስተያየት አለ ። የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ ሰጥታ የምታከብረው እ/ኤ/አ/ ጥር ፮ ቀን የሚለውን የኤጲፋንያን በዓል ነበር ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የጌታን ጥምቀቱንና ልደቱንም ከዚሁ ጋር በማያያዝ ጥር ፮ ቀን ስታከብር እንደቆየች የዕውቀትና የታሪክ መድበል ወይንም እንሳይክሎፒዲያ ይገልጻል ።

በክርስቲያን ዓለም ውስጥ እንዲህ ያለ ልዩነት ሊደርስ የቻለው ከጌታ ልደት በፊት በ፵፮ ዓ. ዓለም ጁሊየስ የተባለው የሮማ ቄሣር የጊዜው የከዋክብት መርማሪ የነበረውን ሶስግንስን አስጠርቶ ተመሰቃቅሎ የነበረውን የዘመናት አቆጣጠር እንዲያስተካክል አዘዘው ።

ይኸም ሊቅ ፈቃደኛ ሆነና እንደታዘዘው አድርጐ ስላቀረበለት ጁሊየስ ቄሣርም በሁኔታው እጅግ ተደስቶ ሊቁን ካመሰገነ በኋላ ሮማውያን ቀድሞ የነበረውን የዘመን አቆጣጠር ትተው ተሻሽሎ የወጣውን አዲሱን የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት ተከትለው ወደፊት እንዲሠሩበት አዘዘ ፤ ዓመቱንም በ፲፪ ወሮች ከፋፍሎ እያንዳንዱን ወር ከየካቲት በስተቀር በማፈራረቅ ፴፩ና ፴ ቀኖች እንዲኖራቸው አድርጐ ወሰነ ።

የየካቲት ወር ግን ፳፱ ቀኖች እንዲኖረው አደረገ ። ነገር ግን በየአራቱ ዓመት አንድ ቀን ትርፍ ስለሚመጣ በአራተኛው ዓመት የካቲት ፴ ቀኖች እንዲኖረው ሆነ ። በተጨማሪም ጁሊየስ ቄሣር የዓመቱ መጀመሪያ መጋቢት የነበረውን አዛውሮ ጥርን የዓመቱ መጀመሪያ እንዲሆን ደነገገ ። የዘመናት አቆጣጠርን ከወራቱ ጋር ለማያያዝና ለማዛመድ በመፈለጉ ጁሊየስ ቄሣር በ፵፮ ዓመተ ዓለም ማለት አዲሱ ድንጋጌ በወጣበት ዓመት ፬፻፵፭ ቀናት እንዲኖሩት አዘዘ ። ሮማውያን ይህን ዓመት ዝብርቅርቅ ዓመት ብለው ጠርተውታል ። ከዚህም በኋላ የዘመኑን መቁጠሪያ ስም የያዘው ጁሊየስ ቄሣር ስለተባለ በእ



ርሱ ስም «ጁሊያን ካላንደር» ተብሎ እስካሁን] ሲጠራ ይኖራል ። የጁሊያንን የዘመን አቆጣጠር ብዙዎች አገሮች ለአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያህል ሲገለገሉበት ቆይተዋል ፤ ምክንያቱም የዓመቱ ቀናት ተቀምረው ፫፻፷፭ ከሩብ ሊሆኑ በመቻላቸው ነበር ። ይህም መሬት ፀሐይን በዓመት አንድ ጊዜ የምትዞርበት የትክክለኛው ቀን ብዛት ነው ። ይህም ሆኖ የተሟላ አልነበረም ፤ ምክንያቱም ፲፩ ደቂቃ ከ፲፬ ሴኮንድ ከሚገባው ጊዜ ስለሚበልጥ ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ በወራት ልውውጥ ላይ አልፎ አልፎ ዝብርቅርቅ ተፈጥሯል ። ስለዚህም ይህንን የወራትን የመፈራረቅ ጊዜ ለማስተካከልና በጠቅላላው የጁሊያንን የዘመን አቆጣጠር ለማሻሻል በ፲፭፻፹፪ ዓ. ም. እ/ኤ/አ/ የሮማው ፓፓ ጐርጐርዮስ ስምንተኛ የከዋክብት ሊቃውንትን ሰብስቦ ከተመካከረበት በኋላ የዘመን አቈጣጠር ተሻሽሎ እንዲሠራበት አዋጁን አስተላለፈ ። ከዚያ በፊት ቤተ ክርስቲያን ጁሊየስ ቄሣር የተባለው የሮማ ንጉሥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፵፮ ተኛው ዘመን በበየነው የዘመን አቆጣጠር ትመራ ነበር ። ነገር ግን ይህ የዘመን አቈጣጠር ጉድለት ተገኘበት ፤ ምድር ፀሐይን በአንድ ዓመት አንድ ጊዜ ለመዞር የሚወስድባት ጊዜና የጁሊየስ ቄሣር ዘመን አቈጣጠር በሚያመለክተው የዓመት ርዝመት አልተስማሙም ፤ እንዲያውም በ፲፭፻፹፪ ዓ /ም እ/ኤ/አ የምድርን መዞር በመከታተል የተገኘው የዘመን ርዝመት በ፲ ቀኖች የተለያዩ ሆነው ተገኙ ፤ ይህንን ጉድለት ለማስተካከል በ፲፭፻፹፪ ዓ/ም እ/ኤ/አ/ጥቅምት ፭ ቀን ሊሆን የሚገባው ቀን ጥቅምት ፲፭ ቀን እንዲሆን ተመድቦ የጐርጐርዮስ ዘመን አቆጣጠር የተጀመረው በዚሁ ዘመን ነው ።

ይህ ሕግ ከወጣ በኋላ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የሚከተሉ አገሮች ወዲያውኑ ተቀብለው በሥራ ላይ አዋሉት ፤ ሆኖም የጀርመን ግዛቶች እስከ ፲፰ኛው መቶ ዓመት ድረስ በቀድሞው በጁሊያን የቀን አቈጣጠር ይጠቀሙ ነበር ፤ እንግሊዝም ብትሆን አዲሱን የጐርጐሪያንን የቀን አቆጣጠር የተከተለችው በ፲፯፻፶፪ ዓ/ም እ/ኤ/አ/ ነው ። ከዚያም ወዲህ ሌሎች የኤውሮጳ አገሮች ተቀብለውታል ።

ይህም ሁሉ ሊሆን የቻለው በ፲፭፻፹፪ ዓ/ ም የተጨመሩት ፲ ቀኖች ተጠራቅመው ጐርጐሪያን በተባለውና ጁሊያን በተባለው የዘመን አቈጣጠር መሐል የዓመታት ልዩነት ስለፈጠረ ነው ። እንዲያውም አሁን በያዝነው ክፍለ ዘመን እያደር ተጨማሪ የሆኑት ቀኖች ወደ ፲፫ ቀን ደርሰዋል ይባላል ።

በዘመን አቆጣጠር ለውጥ የተነሣ የምዕራባውያንና የኢትዮጵያውያን የልደት በዓል በ፲፫ ቀኖች ይለያያሉ ፤ የትንሣኤ በዓል ግን በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ አንድ ላይ ይውላል ። ምንም እንኳ ምዕራባውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን



2*

www.ethiopianorthodox.org

የጁሊያንን የዘመን አቆጣጠር ትከተላለች ብለው ቢገምቱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን በጎርጎሪያንም ሆነ በጁሊያን የዘመን አቆጣጠር ሳትመራ ድሜጥሮስ በ፪፻፲፮ ዓ/ም የወሰነውን ባሕረ ሃሳብ ተከትላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጋቢት ፳፱ ቀን ተጸንሶ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ተወለደ፤ ጥር ፲፩ ቀን ተጠመቀ ስትል ትወስናለች ። ይህም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሆነው በስንክሳር ተጽፎ ስለሚገኝ ሁኔታውን በይበልጥ በዚሁ መጽሐፍ መረዳቱ ሳይጠቅም አይቀርም ።

ይሁን እንጂ በመጀመሪያው እንደተናገርነው ዓለም ብዙ ጊዜ ስለዘመን አቈጣጠር ብዙ ችግር ገጥሞት እንደነበረ ግልጽ ነው፤ ለምሣሌ ከለዳውያንና ባቢሎናውያን ዘመንንም ሆነ ቀናትን ይቈጥሩ የነበሩት በፀሐይ በከዋክብት በጨረቃ ነው እየተባለ ይገመታል ። ኋላም የዕርዕ ሰዎች እነሱ የተወለዱበትን ነገሥታቱ የነገሡበትን ዘመን ለማወቅ ሲፈልጉ በእንዲህ ያለ ማራቶን ተወለድኩ ይህን ያህል ማራቶን ሆነኝ፤ ነገሥታቱም ይህን ያህል ማራቶን ነገሡ እያሉ ዘመናቸውን በማራቶን ይቆጥሩ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ። ከዚህ ሌላ ደግሞ እገሌ በተሾመ ጊዜ እገሌ በነገሠ ወራት ተወለድኩ እያሉ ዘመናቸውን በሹም በንጉሥ ይቈጥሩ ነበር እየተባለ ይታሰባል ።

ኢትዮጵያ ግን በዘመነ ኦሪትም በዓመተ ዓለምም እየቈጠረች ሥራዋን ስታከናውን ቆይታለች ። በዘመነ ሐዲስም ደግሞ ክርስቶስ ከተወለደበት ጊዜ አንሥቶ ድሜጥሮስ የሊቀ ጳጳስነት ማዕረግ አግኝቶ እስከተሾመበት ዘመን ድረስ የአጽዋማትም ሆነ የበዓላት ለውጥ ትክክለኛ ውሳኔ ይዞ ስላልነበር እሱ በተሾመ በ፳፮ ዓመት ጌታችን ኢየሱስ በተወለደ በ፪፻፲፮ ዓ/ም መንፈሳውያን ሊቃውንትንና የከዋክብት አቈጣጠር ችሎታ ያላቸውን ምሁራን በጉባኤ ሰብስቦ በዐቢይ ቀመር፤ በማዕከላዊ ቀመር፤ በንዑስ ቀመር ወስኖ የበዓላትንና የአጽዋማትን አቀነባበር የዘመንን አቈጣጠር በሚገባ አድርጎ ስለወሰነ የዘመን አቈጣጠር ችግር ኢትዮጵያውያንን ገጥሟቸው አያውቅም ። ድሜጥሮስም ይህንን ለመወሰን ያሰበበት ዋናው ምክንያት ስቅለት መጋቢት ፳፯ን ትንሣኤ መጋቢት ፳፱ን ቀን ሳይለቁ በየዓመቱ እየተመላለሱ ይውሉ ስለነበር ከመጋቢት ፳፮ እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ባሉት ቀናት ስቅለት ዓርብን ትንሣኤ እሁድን ሳይለቁ እንዲውሉ በማለት ወሰነ ። የበዓላትና የአጽዋማት ማስገኛ የሆነው መጥቅና ፤ የሌሊትና የመዓልት መቊጠሪያ የሆነው አበቅቴም እነዚህ ሁለቱ ከ፴ እንዳይወጡና እንዳይወርዱ ከደነገገ በኋላ የክርስቶስ ልደት በ፫ቱ ዘመናት በታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንዲውል በ፬ተኛው በዘመነ ዮሐንስ ግን ጳጉሜን ፮ ቀን ስለምትሆን ታኅሣሥ ፳፰ ቀን እንዲከበር አውጀአል ።



በተጨማሪም ዘመናት ቍጥራቸውን ይዘው እንዲመላለሱ በማለት ዐውደ ዓመት በፀሐይ ፫፻፷፭ በአራተኛው ዓመት ግን ፫፻፷፮ ። በጨረቃ ፫፻፶፬ እንዲሆኑ ስለአቀናበረ ዘመናት በዚህ ሲመላለሱ እንዲኖሩ በማድረጉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለዘመናት አቈጣጠር ቀድሞም ሆነ ዛሬ ችግር ገጥሟት ስለማያውቅ የጁሊያንንም ሆነ የጎርጎሪያንን የዘመን አቈጣጠር ሳትከተል ከማንም ሳትበደር በራሷ የዘመን አቈጣጠር ስትመራ የኖረችው ከዚህ የተነሣ ነው ።

ይህንንም ለማወቅ ብንፈልግ አቡሻህር የተባለውን መጽሐፍ ብንመለከት ለመረዳት እንችላለን ።

## ፫ኛ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው ይዞታ

ከሙሴ እስከ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የነበረችው ደብተራ ኦሪትና ሰሎሞንም በልዩ ልዩ ጌጥ አስጊጦ የሠራው ቤተ መቅደስም ቢሆን እነዚህ ሁሉ የበግና የላም የልዩ ልዩ እንስሳት ሥጋና ደም ይሰዋባቸው ስለነበሩና ሊቀ ካህናቱም በዓመት አንድ ቀን ከላይ በተጠቀሱት ሥፍራዎች ገብቶ የሕዝቡን ኃጢአት ያስተሠርይ የነበረው የእንስሳን ደም በማፍሰስና ስብ በማጤስ ስለነበር ሕዝብ እምነቱን የሚያሳርፍባቸው እውነተኛ ድርጅቶች አልነበሩም ። ሊቀ ካህናቱም ቢሆን በሥጋ ልደት ተገልጾ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለሚያቀርበው ለትክክለኛው ሊቀ ካህናት ተመሣሣይ ነበር እንጂ እርግጠኛው ሊቀ ካህናት አልነበረም ። ለዚህም መረጃ የሚሆነን ክርስቶስ በልደት ከመገለጹና እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከመቋቋሟ ቀደም ብሎ በነበረው ዘመን የሚኖሩትን አሕዛብ ሁሉ ደብተራ ኦሪትም ቤተ መቅደስም ይጸየፏቸው ነበር ። በተጨማሪም ከእሥራኤልም ሕግና ሥርዓት የተለዩ ከተስፋውም ኪዳን ውጭ ከመሆናቸው የተነሣ ተስፋ አልነበራቸውም ። ክርስቶስ በልደት ተገልጾ ራሱ መሥዋዕት ሆኖ ያቋቋማት የወንጌል ቤተ ክርስቲያን ግን ቀርበው የነበሩት እሥራኤል ከተስፋው ውጭ ሲሆኑ ርቀውና በእሥራኤል ዘንድ ተጠልተውም የነበሩትን አሕዛብን ተቀብላ የክብሩ ወራሽ እንዲሆኑ አድርጋቸዋለች ።

ከዚህም የተነሣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚገኝ መሆኑን በወንጌል አማካይነት ገልጿል ። በልደቱም ጥላ ሥር ተዘግተው ለሚኖሩ ምዕመናን ለሥጋቸውና ለነፍሳቸው ዕረፍትን ለሚፈልጉ ሁሉ አገልግሎቷን ለሕዝብ እንድታበረክት በማለት ወደ እርስዋ የሚገባ ሁሉ እንዲጠቀምባት በማሰብ የመንፈስ ማደሻ የምትሆን አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የዕረፍት ድርጅት ትሆንላቸው ዘንድ አቋቁሞላቸው ። እንግዲህ



www.ethiopianorthodox.org

ልደት በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው ይዞታ የተሟላ በመሆኑ ክርስቶስ የተወለደባት ቤተ ልሔም የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በሥጋ ተገልጾ ለዓለም ያደረገውን ሰፊ ልግሥና በየዓመቱ የልደቱን በዓል ራሷ እያከበረች ምእመናንን ስታስከብር ትኖራለች ።

## ፩ኛ ከሕዝብ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት

የክርስቶስ ልደት በዓል በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ክርስቲያኖች በዓመት ከሚያ ከብሯቸው በዓላት ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ነው ። በዓሉ የሚከበረው በዚያን ጊዜ በቤተ ልሔም ውስጥ የነበረውን ሥነ ሥርዓት በመከተል ጠቢባን ለቤተ ልሔሙ ሕፃን ባቀረቡት ወርቅ፤ዕጣንና ከርቤ ስጦታዎች አምሳያ ነው ።

በዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች የልደትን በዓል በአንድ በተወሰነ ዕለት እንደሚያከብሩት ሁሉ ስለበዓሉ ታላቅነት የሚያደርጉት ሥነ ሥርዓትም እንደ የሀገሩ ልማድ የተለያየ ነው ።

በኢትዮጵያ ገና ከዋዜማው ጀምሮ የአከባበሩ ሥነ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ይጀመራል ። ከምሽቱ አራት ሰዓት ሲሆን የጌታን መወለድ የምሥራች የሚያበሥሩ የአብያተ ክርስቲያናቱ ደወሎች በያሉበት ድምፃቸውን ካሰሙ በኋላ ፤ ሕዝቡም ካህናቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይገሰግሣሉ ።

ከዚያም በኋላ ካህናቱ ማኅሌት ቁመው ክርስቶስ ተወለደ በምድርም ሰላም ሆነ እያሉ ሲዘምሩ ሴቶቹም ወንዶቹም ተባብረው ሲያመሰግኑ ይቆዩና ቅዳሴ አስቀድሰው ልክ ከሌሊቱ ፱ ሰዓት ሲሆን ከዚህ ላደረሳቸው አምላክ ምስጋና እያቀረቡ ወደየቤታቸው ይሔዳሉ ። ከነጋም በኋላ ዘመድ በመጠየቅ ቤተ ሰብ በመሰብሰብ ግብዣ በመገባበዝ ልዩ ልዩ ስጦታ በመለዋወጥ ቤታቸውን ቄጤማ ፤ ፈላ በመጐዝጐዝ ፤ ዳቦ በመጋገር ጠላ በመጥመቅ ጠጅ በመጣል በግ ፤ ዶሮ ፤ በማረድ ከአካባቢ የሚገኙትም ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው ሰንጋ ጥለው በመቃረጥ በዓሉን ያከብሩታል ። በየቤታቸውም ምሳ በሚበሉበት ጊዜ በመሶብ ተሠርቶ ተሸፍኖ ከመሐል ይቀርባል ። በመሶቡም ዙሪያ ለመቀመጫ የሚያገለግሉ በርጩማዎች ይደረደራሉ አለዚያም በመሶቡ ዙሪያ የበግ አጐዛ ወይም ጀንዲ ይነጠፋል ፤ ሁሉ የሀገር ልብስ ለብሰው በመሶቡ ዙሪያ ተሰብስበው ይጋበዛሉ ። ከበሉና ከጠጡ በኋላ ወደ ሜዳ ሄደው የፈረስ ጉግስ ፤ የገና ጨዋታ ሲጫወቱ ይውላሉ ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከጥንት ጀምሮ ከአባቱ ሲያያዝ በመጣው በእንዲህ ያለው የልማድ ግንኙነት የገናን በዓል ከትንሽ እስከ ትልቅ ሲያከብረው ይኖራል ።



## በሌላው ክፍለ ዓለም ደግሞ እንደሚከተለው ነው

በአሜሪካ) በዓሉ ከመድረሱ በፊት ለቤተ ሰብ ለዘመድ ለወዳጅ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ቀደም ብለው ሲዘጋጁ ይሰነብቱና በዓሉ ሲደርስ ፫ ቀን ወይም ፩ ቀን ሲቀረው የተዘጋጁት ስጦታዎች ሁሉ መታደል ይጀመራሉ ። መንፈሳዊ ስሜት ባለበት በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መዝሙር በመዘመር ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ይከበራል ። ለምሳሌ ያህል በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በቅጥር ግቢው ውስጥ በጥጥ አመልማሎ ተፈነጣጥቆ በአጌጠ ከር ሻማ ያለበት ዛፍ ይተከላል ፤ በአጠገቡ የቤተ ልሔሙን ግርግም የመሰለ ምስል ወይንም እውነተኛ ከብቶችም የሚገኙበት በረት ተሠርቶ በሕዝብ ለብዙ ጊዜ ይጐበኛል ።

## በ ፈ ረ ን ሣ ይ

ይህን በመሰለ ሥነ ሥርዓት ይከበራል ፤ በተለይ ሕፃናትና ልጆች ማታ ሕፃኑ ክርስቶስ በረድኤቱ ጫማዎቻቸውን እንደሚመላላቸው በመተማመን መጫሚያቸውን ከጉበኑ ጥግ ያኖሩታል ።

## በ ስ ዊ ዘ ር ላ ን ድ

ደግሞ በሚያስደንቅ ሁኔታ የሚከበር ሲሆን ከሌላው ትንሽ ለወጥ የሚልበት ልጃገረዶችም ሆኑ ወንዶች ልጆች ለገና ዋዜማ በሚሄዱባቸው ቤተ ክርስቲያኖች መግቢያ አጠገብ ከሚያገኟቸው ምንጮችና እንዲሁም ቧንቧዎች ሦስት ሦስት ጊዜ ይጐነጫሉ ምክንያቱም እጮኞቻቸውን በጐዳና ወይም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እናገኛለን እያሉ ስለሚያምኑ ነው ። ከዚህም ሌላ አንዳንድ ስዊዞች የልደት ማታ እንስሳት አፍ አውጥተው በመናገር ለክርስቶስ ክብር ይንበረከካሉ ብለው ያምናሉ ።

## በ ኢ ጣ ል ያ

ከልደት በፊት ያለውን ቀን ገሃድ ነው በማለት ይጾሙታል፤ወደ ማታም በተዘጋጀ በቤተ ልሔም ሥነ ሥርዓት ያከብሩታል ። ሌላው አከባበር ግን ከሌላው አገር ልዩነት የለውም ።

## በ እ ስ ፓ ኝ

የገና በዓል መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ማታ ከተከበረ በኋላ ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ ሕዝቡ በጭፈራና በዳንስ ሌሊቱን ያነጋል ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚሁ ቀን የሚደሰቱበትም ሙዚቃ ጀታ ሲባል ይህም ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ ከቅድም አያቶቻቸው ሲያያዝ የመጣ በመሆኑ ሁሉም ይደሰቱበታል ።

## በ እ ስ ካ ን ዲ ኒ ቪ ያ

ሕዝብ ደግሞ ክርስትናን ከመቀበሉ ቀደም ብሎ ያመልክ የነበረ በለመለመ ዛፍ ስለነበር ክርስትናንም ከተቀበለ ወዲህ ለክርስቶስ ልደት መግለጫ አድርጐታል ።

## በ እ ን ግ ሊ ዝ

የክርስትና ታሪክ ውስጥ እንደሚነገረው ዊንፍሪድ የተባለው የወንጌል መልእክተኛ እ/ ኤ/ አ/ ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ዓመታት በፊት ወደ ሰሜን ጀርመን ለስብከት ሲዘዋወር በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ አረማውያን ልዑል አሰሉፍ የተባለውን መስፍን እንደ ሀገራቸው ልማድ ከትልቅ የወርካ ዛፍ ሥር ቶር ለተባለው ጣዖት ሊያርዱ ሲያጋድሙት ደረሰ ፤ ይህም ወንጌላዊ የሰብአዊው ፍጡር ደም በከንቱ እንዳይፈስ አውግዞ መሥዋዕት ሊሠዋ በተዘጋጀበት አካባቢ በጉልህ ደምቆ ይታይ የነበረ አንድ የወርካ ዛፍ ቆርጦ በቅጽበት ከወርካው ጉቶ አያሌ ቀንበጦች ያሉት የጥድ ተቀጥላ ወጣ ፤ ዊንፍሪድ የክርስቶስን ልደት በአዲስ ወጥ ጥድ መሰል ለአረማውያኑ አስረዳ ፤ ከዚያን ቀን ጀምሮ ጥድ የልደት ዛፍ ተባለ ይባላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የልደት በዓል በጥድ መከበር የተጀመረው በስምንተኛው መቶ ዓመት በምሥራቅ ፈረንሣይ አውራጃ ነው ይባላል ። በጠቅላላ በዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ የልደትን በዓል እንደየሀገራቸው ባሕልና ልማድ ስለሚያከብሩት የገና በዓል ከሕዝቡ ጋር ያለው የልማድ ግንኙነት በእንዲህ ያለ ሁኔታ ነው ።

## ፫ኛ ሊደረግ የሚገባ መሻሻል

ስለ ክርስቶስ ልደት በክርስቲያኖች ዘንድ የሚደረገው መሻሻል በይበልጥ ሥጋዊውን እንጂ መንፈሳዊውን የተከተለ መስሎ አይታይም ፤ ምክንያቱም የገና በዓል የሚከበረው ጫወታ ለመጫወት ልዩ ልዩ ስጦታ ለመለዋወጥ አዳዲስ ልብሶችን በየዓይነቱ ገዝቶ ለብሶ ለመንሸራሸር ይመስላል እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወት በኩል አዲስ ለውጥ ለማግኘት መፈለጉ እየቀረና በዓሉም የመንፈሳዊ በዓል መሆኑ ጥቂት በጥቂት እየተዘነጋ በመሔድ ላይ ነው ። አንዳንድ በስም ክርስቲያን ሆኖ የሚኖረው ግዴለሽ ሁሉ በሌላ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሳይደርስ ይቆይና ከምዕመናንም ጋር ተባብሮ በጸሎትም ሆነ በቅዱስ ቊርባን ተካፋይ ሳይሆን ይኖርና ማኅበራዊ ኑሮ ስለሚያስገድደው በዓመት አንድ ቀን በዓሉን ለማክበር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል ። እንዲህ ያለውም ሁኔታ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ ለኑሮው መሻሻልን ለሕይወቱ ደስታን ሊፈጥርለት አይችልም ። እንዲህ ያለውም ሰው በዓሉን የሚያከብረው መንፈሳዊ ደስታን ያስገኝልኛል በማለት ሳይሆን በዚህ ቀን ምርጥ ምግብ ስለሚበላና ዝና ያለው መጠጥ ስለሚጠጣ የስጦታም ልውውጥ ስለአለ ለደስታው ሲል በክርስቲያን ስም የሚጠራው ሁሉ ያከብረዋል ።

እንዲህ ያለውም አድራጐት ራስን በራስ ማታለል በመሆኑ የበዓሉ መንፈስ ወደ አክባሪው ልብ ገብቶ የሚያርፍበት ሥፍራ የለውም ፤ እንዲያውም በተዘዋዋሪ መንገድ ጸጸት እየሆነ የሕሊናም ወቀሳ ያሳድርበታል ።

ይሁን እንጂ ሁኔታውን በጠቅላላው ጠለቅ ብለን የመረመርነው እንደሆነ በዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ ረዘም ላለ ጊዜ ይዘውት በቆዩት ባሕላዊ ቅርሳቸው ላይ ጠቃሚ ያልሆነውን ልማድ ተክተውበታል ።

በተጨማሪም የምዕራባውያን የገና አከባበር በሰው ሠራሽ ጉዳዮችና በዓይን በሚታዩ በእጅ በሚጨበጡ ዕቃዎች ብዛትና ፍጹም በሆነ ሥጋዊ ደስታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ መንፈሳዊ የሆነውን የበዓሉን መልክ ለቆ እናገኘዋለን ። ሰው በሥጋው ብቻ እየተሻሻለ በመንፈሱም ጭምር የማይሻሻል ከሆነ ድካሙ ሁሉ ዋጋ ያለው አይሆንም ።

ይህንንም ስንል ደግሞ ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ኑሮ አሻሽለው ከሥጋዊ ጌጥ ይልቅ መንፈሳዊ ጌጥን የሚመርጡና በዓሉንም ከልብ የሚያከብሩ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም ።

## ፬ኛ ማ ጠ ቃ ለ ያ

ከአንድ እስከ አምስት ያሉትን ነገሮች አንድ በአንድ መርምረናቸዋል ። በክርስቲያኖች መካከል አለመግባባት ሊደርስ የቻለው በጌታ መወለድ ቀንና ዘመን ምክንያት መሆኑን ተረድተናል ። ነገር ግን እንዲህ ያለው ሁኔታ በአንድ አምላክ ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ቀላል እንጂ ከባድ ነገር አልነበረም ። እስከዚህም ድረስ ሊያለያዩና በመካከላቸውም አለመግባባትን ሊፈጥርባቸው ባልቻለም ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

ይልቁንስ በየጥቃቅኑ ነገር መለያየታቸውን ትተው ከጠላቶቻቸው ዘንድ የሚወረወርባቸውን ነገሮች ተባብረው እየመከቱ የወንጌል ብርሃን በዓለም ላይ ሁሉ እንዲበራና የአረማውያንም ኃይል በትምህርት እንዲቀነስ ለአንድ ዓላማ ቢደክሙ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ አማካይነት ለሰው ልጆች ያደረገው ሰላም በይበልጥ እየነገሠ እንደሚሄድ እርግጥ ነው ።

ይሁን እንጂ የአከባበሩን ሥነ ሥርዓትና የቀኑንም ልዩነት እንደታላቅ ቁም ነገር ቆጥሮ መለያየት ባላስፈለገም ነበር ። የልደት በዓል አከባበርም መንፈሳዊ ዝንባሌንና የማኅበራዊ ኑሮን መልክ ከያዘ በባሕልም ሆነ በቀን ልዩነት ያለው አኳኋን እስከዚህ ድረስ ከፍተኛ አስተሳሰብ ሊሰጠው እንደማይገባ ግልፅ ነው ። በዚያም ሆነ በዚህ ክርስቲያኖች በየጥቃቅኑ ነገር መለያየታቸውን ትተው እርስ በእርሳቸው እየተግባቡ ክርስቶስ ስለ ፍቅር ስለርኅራኄ ስለፍርድ ስለቸርነት በጠቅላላው ስለማኅበራዊ ኑሮ ስምምነትና ስለሌሎችም ባሕርያት ያስተማረውን ትምህርትና ምሳሌ ቢከተሉ ኑሮ ይህች ዓለም በሰላምና በምቾት እረገድ የሚጐድላት ነገር ሊኖር ባልቻለም ነበር ።

ከዚህም ሌላ ደግሞ አሁን በአለንበት ዘመን በብሔራዊ በዓሎች አከባበር በኩል የሚያሳስበው የክርስቶስ የልደት በዓል አከባበር ከመንፈሳዊ ዝንባሌ ፈቀቅ እያለ የልዩ ልዩ ሸቀጥ ማንሻና የማቴሪያል በዓል እየሆነ ከመሔዱም በላይ የልደት ምሽት የመዝሙር የምስጋና የጸሎት ምሽት መሆኑ ቀርቶ የዳንስ የጭፈራ የስካር ምሽት እየሆነ በመሔዱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህ ሁኔታ እየተስፋፋ ከመሔዱ በፊት ሊያስቡበት ይገባል ።

ከነቢየ ልዑል ዮሐንስ ፤



# በ ዓ ለ ሃ ም ሳ

ሊቃውንቱ እንደሚያብራሩት በዓለ ሃምሳ ማለት ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ ዋዜማ የሚገኙት ከዐርባ ዘጠኙ ቀናት ለጥቆ የሚውል የአምሳኛው በዓል ማለት ነው እንጂ አምሳው ቀን በመላ በዓል ነው ማለት አይደለም ። በዓለ ሃምሳ የሚለው ቃል በጽርዕ ቋንቋ ጰንጠቆስጤ ይባላል ፤ ይህም የሰባት ሳምንታት መጨረሻ በዓል ማለት ነው ።

## የት መጣው በታሪክ መልክ

የበዓለ ሃምሳን የት መጣ ስናገር የበዓላትንም አመጣጥ መግለጽ አስፈላጊ ሁኖ ስላገኘሁት የሁሉንም የትመጣ ለመናገር እሞክራለሁ ። በመጀመሪያ የሥነ ፍጥረት ጌታ እግዚአብሔር ስድስቱን ቀናት ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛው ጨርሶ እንዳረፈ ስለምንረዳ በዓል እንዲከበር የመጀመሪያውን መሠረት የጣለው ራሱ እግዚአብሔር ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ልናገኝ አንችልም ። ከዚያም ቀጥሎ ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን የ ሚሠራበትና የሚቀጣበት ፤ የሚያስተዳድርበት ሕግ አጥቶ ፍላጐቱን ይሰጠው ዘንድ ልመናውን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ ። እግዚአብሔርም ልመናውን ሰምቶ ወደ ደብረ ሲና ወጥቶ አሠርቱ ቃላትን እንዲቀበል አደረገው ፤ ከተቀበላቸውም አሰርቱ ቃላት ሦስተኛው በዓል ማክበር ሆኖ እናገኘዋለን ዘፀዓ ፳ ፤ ፰ ። ይሁን እንጂ በዓሉ በዚህ ብቻ አልተወሰነም ፤ ሌሎችም በዓላት ነበሩ አሁንም አሉ ፤ በአከባበራቸውም የግል ድርጊታቸውን ይዘው የሚጓዙ እንጂ ከማንም ጋር አይቀላቀሉም ነበር ፤ እነርሱንም እንደሚከተለው እንገልጻለን ። እግዚአብሔር ግብረ ፍጥረታትን ፈጽሞ ያረፈበት ዕለት በየሳምንቱ ይከበር ነበር ፤ ዛሬም ቢሆን ይከበራል ። በተጨማሪም በዓለ መጥቅዕ ወይም የዘመን መለወጫ ፤ በዓለ መጸለት ፤ በዓለ ፍሥሕ ፤ በዓለ ሠዊት ፤ የሚባሉ በዓመት አንድ አንድ ቀን የሚከበሩ በዓላት ነበሩ ። እንዲሁም በሰባተኛው ዓመት የሚከበር ዓመተ ኅድገት የሚባል በዓልም እንደነበር ይነገራል ። ይህም ስድስቱን ዓመታት በሙሉ ተግተውና በርትተው ሠርተው በሰባተኛው ዓመት ሥራቸውን ትተው የሚቀመጡበትና የሚያርፉበት ስለሆነ እንኳን ሰዎች በቤት የሚገኙ እንስሳትም ሆኑ የ ሚያርሷት መሬት ሳትቀር ታርፍ ነበረች ። ደግሞም ከነዚህ ሌላ ዓመተ ኅድገትን በሱባኤ ቆጥረው በሀርባ ዘጠኝ ዓመት የሚያከብሩት ኢዮቤልዩ እየተባለ የሚጠራ ታላቅ በዓል ነበራቸው ፤ እንዲሁም



www.ethiopianorthodox.org

ሠረቀ ፀርነን (መባቻን) እየተመለከቱ የሚያከብሯቸውም በዓላት ነበሯቸው ፤ ለተጠቀሱት በዓላትም ማብራሪያ ይሆን ዘንድ የሚቀጥለውን ጽሑፍ እናንብ ።

## ሀ· በ ዓ ለ ፍ ሥ ሕ

እስራኤል በምድረ ግብፅ በባርነት እየተገዙ ሲኖሩ ሳሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከባርነት ቀንበር አውጥቶ ወደ ምድረ ርስት ስላገባቸው ፤ ከባርነት ቀንበር ነፃ የወጡበትን ቀን በዓለ ፍሥሕ እያሉ በየዓመቱ እንዲያከብሩ ታዝዘው ነበር ፤ ዘፀዓት ፲፪ ፲፰—፳ ። በኋላ ከዩአቂም ጀምሮ የባቢሎንና የፋርስ የአሶርም መንግሥታት ወደ ኢየሩሳሌም እየዘመቱ አገሩን እያጠፉ ሕዝቡን እየማረኩ ሲወስዱዋቸው ይኖሩ ነበርና አገራቸው በመጥፋቱና በመማረካቸው እያዘኑ ኢየሩሳሌምንና ሌሎችንም የኢየሩሳሌምን አውራጃዎች ትተው በየሀገሩ እየተሰደዱ ንግድ እየነገዱ ሌላም ልዩ ልዩ የእጅ ሥራ እየሠሩ ይኖሩ ነበር ። ይህም ሆኖ እጅግ በጣም የጸና ችግር ካልገጠማቸው በቀር በዓለ ፍሥሕን በኢየሩሳሌም እንዲያከብሩ ታዝዘው ነበርና በየሀገሩ ከተበታተኑት ሕዝበ አይሁድ ባለገንዘብ የሆኑት በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም እየወጡ በዓለ ፍሥሕን ያከብሩ ነበር ። ለመውጣት የማይችሉት ግን ከየማኅበራቸውና ከየምኵራባቸው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች እየመረጡ ይልኩ ነበር ፤ በዓለ ፋሲካን ካከበሩ በኋላ ደግሞ አምሳ ቀናት ቈጥረው በዓለ ሠዊት የሚባለውን በዓል አክብረው ወደየመጡበት ሀገር ይመለሱ ነበር ።

## ለ· በ ዓ ለ ሰ ዊ ት

ሰዊት ማለት የሸት በዓል ማለት ነው ። ይህም እህል የሚታጨድበት የመከር ወራት ሲጀመር የሚከበር በዓል ነው ። የኢየሩሳሌም ክረምት መግቢያ በኅዳር ወር ስለሆነ መከር የሚደርሰውና አጨዳው የሚጀመረው ከሚያዝያ ወር እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ነው ። መከርም በደረሰ ጊዜ መጀመሪያ ከሚወቁት እህል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ «እንዲሰጡ» ታዘው ነበር ።

ይህንኑም ከበዓለ ፋሲካ ጀምሮ ሰባት ሳምንቶች እስኪፈጸሙ ድረስ እያንዳንዱ በየቀኑ አንዳንድ መሥፈሪያ (ጐምር) እህል ይሰጡ ነበር ። ሰባት ሳምንቶችም ዐርባ ዘጠኝ ቀናት ይሆናሉ ። እንግዲህ አንድ ሰው የሚሰጠው እህል ዐርባ ዘጠኝ መሥፈሪያ ይሆናል ማለት ነው ። በአምስተኛውም ቀን ሊቀ



ካህናቱ ከእህሉ በዕንቀብ አቅርቦ ከጸለየበት በኋላ የበጉን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስለሚያቀርብ ይህ ቀን ታላቅ በዓል ሆኖ ሲከበር ይውል ነበር ፤ ዘሌዋውያን ፳፫-፲-፲፯ ። ይህም ዛሬ በሀገራችን የዘመን መለወጫ ዕለት ሁለት ወይም ሦስት መገበሪያ (መሥፈሪያ) ስንዴ በዕንቅብ ቀርቦ የተማረው ሊቅ ባሕረ ሐሳቡን ተናግሮ ሲጨርስ ስንዴውን የሚባርከው ከዚህ ከበዓለ ሰዊት ሲያያዝ የመጣ የአይሁድ ባህልና ልማድ ነው በማለት አንዳንድ ሊቃውንት ይናገራሉ ።

## ሐ· በ ዓ ለ መ ጸ ለ ት

በዓለ መጸለት ብዙ ፍች እንዳለው ይነገራል ፤ አንደኛ የተደራረበ በዓል ማለት ነው ። ይህንንም ሊያሰኘው የቻለው አይሁድ በዓለ መጸለትን ሳያከብሩ በዓለ ፋሲካን አያከብሩም ነበርና አንድ ጊዜ አንድ አስቸጋሪ ጉዳይ ገጥሞአቸው ስለነበር በዓለ መጸለትን አስተላልፈው ከበዓለ ፋሲካ ጋር አብረው ስላከበሩት መሆኑ ይነገራል ፤ ሁለተኛ ደግሞ ከበዓለ ፋሲካ ጋር በአክብሮት ስለተመሳሰለ ነው ፤ በዓለ መጸለትን ሲያከብሩ ዳስ ሠርተው ጋን ተክለው ብዙ ሰው ሰብስበው ነበር ፤ ፋሲካንም ሲያከብሩ እንዲሁ አድርገው ነበር ፤ በሌላ አስተያየት ደግሞ የቂጣ በዓል ማለት እንደሆነ ይነገራል ።

## ፫ በዓለ ሃምሳ በቤተ ክርስቲያናችን ያለው መልክ

ቤተ ክርስቲያናችን በኦሪት ዘመን በእስራኤል ልማድ ይከበሩ የነበሩትን በዓላት ፈጽማ አልተወቻቸውም ፤ በሁሉም በዓላት አዳዲስ በዓላትን ተክታ ስታከብር ትገኛለች ፤ አተካኳም እንደ ሚከተለው ነው ።

በበዓለ መጥቅዕ—ቅዱስ ዮሐንስን (ዘመን መለወጫ)

በበዓለ መጸለት—ልደትንና ጥምቀትን

በበዓለ ፍሥሕ—ፋሲካን

በበዓለ ሰዊት—ጰራቅሊጦስን ተክታለች ። አሁን በእኛ ዘንድ በዓለ ሃምሳ ወይም ሃምሳኛ ቀን በጽርዕ ቋንቋ ግን ጰንጠቆስጤ ተብሎ በሚጠራው ዕለት በዕለተ እሁድ ከነግሁ አንድ ሰዓት ሲሆን በሐዋርያት ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ በማያውቁት ቋንቋ ይናገሩ ጀመር ፤ የዚህን ጊዜ በበዓሉ ሥፍራ ተገኝተው የነበሩት ሕዝብ የሐዋርያትን ሁኔታ ተመልክተው እያደነቁ ወደየሀገራቸው ሲመለሱ ግዙፋን አእምሮ የነበሩት ሕዝብ ደግሞ በሐዋርያት



www.ethiopianorthodox.org

ላይ እያፌዙ ይናገሩ ነበር ። የሐዋርያት ሥራ ፪ ፤ ፳ ፤ ይህንን መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ዕለት መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን አሁንም ቢሆን ታከብረዋለች ። ይሁን እንጂ በዓለ ሃምሳ ተብሎ እንደመጠራቱ በጠቅላላ ታከብረዋለች ማለት አይደለም ። ከዚህ ውስጥ የምታከብራቸው ዕለታት የተወሰኑ ሁነው እናገኛቸዋለን ። እነዚህም እንደ ሚከተሉት ናቸው ። ፋሲካ ከትንሣኤ «እስከ ስምንት ቀናት» እስከ ዳግም ትንሣኤ በዐርባኛው ቀን ዕርገት ፤ በአምስተኛው ቀን ጰራቅሊጦስ ናቸው ። ሀምሳው ቀን ግን በመብልና በመጠጥ እንጂ በሌላ በኩል ሊከበር አይገባውም በማለት ታስተምራለች ። ስለዚህም የዐርብና የሮብ አጽዋማት በነዚህ ሃምሳ ቀናት ተሽረው እናገኛቸዋለን ። ይህም አያሌ ጥያቄዎችን በየጊዜው ያስነሳል ፤ ለዚህም ሊቃውንት ሲመልሱ በዐቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙ እሑድና ቅዳሜ እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ስለማይጾሙ ለእነዚያ ምትክ ነው ፤ የሚለውን አስተያየት ያቀርባሉ ።

እንደዚህ ያለውን ልማድ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አውጥተውና አውርደው ጥቅሙንና ጉዳቱን አመዛዝነው በጉባኤ የደነገጉት አይመስልም ። በበዓለ ሃምሳ ጾም አትዋሉ ፤ ዘር አትምተሩ ፤ የሚል አነጋገር አለ ። ስለዚህም ያለው ከገንዘቡ የሌለው ተጋድሞ ቢሆን በዚህ ሰሞን ጠዋት አፉን ሳይሽር ከቤቱ የሚወጣ የለም ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አምሳው ቀን እንደ ትንሣኤ ነው ይላሉ ።

ይህንንም ማለታቸው ሁሉንም እንደ ትንሣኤ እናክብራቸው ማለታቸው ሳይሆን ዓርብንና ረቡዕን ሳንለይ እንመገብ ማለታቸው ሳይሆን አይቀርምያም ሆነ ይህ አሁን በቤተ ክርስቲያንና በሕዝቡ ዘንድ ያለው መልክ የተለያየ ይመስላል ። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን አምሳኛዪቱ ቀን ብቻ እንድትከበር ስታስተምር ሕዝቡ ግን አምሳ ቀን በሙሉ እንደሚከበር አድርጎ ስለሚገምት ነው ።

## ከሕዝቡ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት

ሕዝቡ ይህንን ልማድ ከጥንት ጀምሮ ስላጠናው አልዘነጋውም ፤ አሐቲ ፋሲካ የሚለውንም አነጋገር ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በመጠኑ ይጠቀምበታል ። ምንም አምሳው ቀን እንደ ፋሲካ ዕለት ይከበር ነበር ብሎ በቃል ሲነገር ቢሰማም ሁሉንም አጣርቶ ተገቢ መስሎ የታየውን ይዞ በመረመድ ላይ ይገኛል፤በከተማ የሚኖረው ሕዝብ



ሁለት ቀን ብቻ የሚያከብር ሲሆን በገጠር የሚገኘው ሕዝብ ደግሞ ስምንቱን ቀን በሙሉ ያከብረዋል ። አከባበሩም ድግሥ ደግሶ እርስ በእርስ ግብዣ በመጠራራት ሥርግ በማሠረግ ዘመድን አክፋይ ይዞ በመጠየቅ ዛሬ ከእኔ ቤት ጠርቼሃለሁ ፤ ነገ ካንተ ቤት በሚቀጥለው ደግሞ ከሌላው እንሔዳለን እየተባባሉና ሌላም ልዩ ልዩ መገናኛዎች በመፍጠርና ገበጣንም በመጫወት የሚያሳልፉት በመሆኑ ይህ በዓለ ሃምሳ የሚባለው ወቅት በሕዝቡ ዘንድ ወርኃ ድግሥ ነው ለማለት ይቻላል ። ይህ ሰሞን ዓርብና ረቡዕ እንደ እሑድ ቅዳሜ መብላታቸው እስከ ዘጠኝ እስከ አሥራ አንድና እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ጹሙ የሚለው ትእዛዝ ተለውጦ ጾም አትዋል ማልደህ እህል ቅመስ የሚል ቃል ስለሚነገር በሕዝቡ ዘንድ ታላቅ ትዝታ ያለው ክፍለ ጊዜ ሊጋብቻ ሆነ ለግብግር ከዚህ የተመቸ ሰሞን ባለመገኘቱ ሕዝቡ ሁሉ ጉዳዩን ሲፈጽም የ ሚታየው በበዓለ ሃምሳ ነው ።

## ጥ ቅ ሙ ና  ጉ ዳ ቱ

በዓለ ሃምሳ ካወቁበት እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ። ግን አንዳንድ ሰዎች ጥቅሙንና ጉዳቱን የተረዱት አይመስሉም ፤ በበዓለ ሃምሳ ጦም አትዋሉ ተብሏል እያሉ ሥራቸውን ቾል ብለው ሌት ተቀን በመብላትና በመጠጣት የክረምት ቀለባቸውን እስከ ሥሩ አሟጠው ጨርሰው የሚመጣውን ወር በባዶ አንጀታቸው ለመጋፈጥ የሚሞክሩ ሞልተዋል ።

እንደዚህ ያለው ይዞታ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ሊታሰብበት የሚገባ ታላቅ ነገር ነው ። የሚቀጥለው ወራት ቅጠል እንጂ ፍሬ የማይታይበት የዓመት ቀለብ ከርሠ ምድር ተደግሶ የሚወለድበት በመሆኑ ታታሪው ሠራተኛ ከመሬት ጋር ለመታገል የሚያስችለውን በቂ ምግብ ማግኘት ስላለበት ቀደም አድርጎ ምግቡን ማደራጀት አለበት እንጂ በበዓለ ሃምሳ ፈጽሞ በሚቀጥለው ወር በቅጠላ ቅጠል ምግብ ለመኖር መጣር የለበትም ፤ በየሀገሩ ብዙ ተድላና ደስታ ይደረጋል ፤ ብዙ ሠርግ ብዙ ግብዣዎችም ይፈጸማሉ ፤ እንዲሁም የሙታን መታሰቢያም ይደረጋል ። ይዞታው አይከፋም ፤ ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው ዘመነ ትንሣኤ በመሆኑ ሁሉም ደስታውን በልዩ ልዩ ምክንያት ቢገልጽ አይነቀፍም ። ግን ለደስታው ወሰን እንዲኖረው ያሻል ። ለዩስታው ጊዜ ካልሰጠው የቀበሮዋ ምሳሌ ይሆናል ፤ «ቀበሮ ማዝሟ ያገኘች እንደሆነ ከደስታዋ ብዛት የተነሣ ያገኘችውን ትቷ ስትፈነጥዝ ቆይታ ስትመለስ ጠፍቷት ይቀራል ይባላል » ግን እንዳገኘች ዝላይ ሳታብዛ በትዕግሥት ብትመገበው ኑሮ ባክና አትቀርም ነበር ። አንዳንድ ሰዎች በእርሱዋ ባሕርይ የተለከፉ



www.ethiopianorthodox.org

አሉ ። ባገኙ ጊዜ ለነገ ለሳልስት አይሉም ። ሌት ተቀን ውቂው ደባልቂው በማለት ለብዙ ጊዜ የሚበቃውን በአጭር ጊዜ ይጨርሱና ከችግር ላይ ወድ ቀው ሲጨነቁ ሲጠበቡ ይታያሉ ፤ ይህ እንዳይሆን ሁሉም በመጠኑ መሆን አለ በት ። በበዓለ ሃምሳ አለመመገብ ሕግ አይደለም ። ጥሪትንም መሚጠጥ ደግሞ ከችግር ላይ ይጥላል ፤ ስለዚህ ጥቅሙንና ጉዳቱን አውቀን ለመኖር እንበርታ ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

«ሕግን የሚሠሩት ይከበራሉ እንጂ የሚሰሙት ወይም በመስማት ብቻ አይጸድቁም» ብሎ ሐዋርያው የተናገረውን ቃል ልንዘነጋው አይገ ባንም ፤ «መጽሐፍን አዘውትሮ የማያነብና ሬዲዮን ተግቶ የማያዳምጥ የዘመ ኑን ሁኔታ ለመከታተል አይችልም» ብሎ አንድ ሊቅ ተናግሯል ። በእርግጥ እነ ዚህን ነገሮች የማያዘወትር ሰው ከዓለም ውጭ ነኝ ይበል እንጂ ከዓለም ውስጥ ነኝ ብሎ መናገር አይገባውም ። አሁንም ዓላማችንን አንዘንጋ ፤ የተነሣንበትን በድጋ ሚ በማስታወስ ፋሲካችንን በዓላችንን በሚገባ እናክብር ፤ በዓለ ሃምሳም ምን ማለት እንደሆነ በጽሑፍ አማካይነት እየተመራመርን እንወቅ ፤ የሚጠበቁትን ባህልና ልምድ መነሻ አለማወቅ በጭንጫ ላይ በቅሎ ፀሐይ ሲወጣ እንደ ሚ ደርቅ ቅጠል መሆን ነውና ለማወቅ መጠየቅ ለመረዳት ማንበብ ያስፈልገናል።

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# የ ማ ተ ብ ማ ሠ ር ል ማ ድ

## መ ግ ቢ ያ

ማተብ (ማዕተብ) አንደኛው ፍች ምልክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቡራኬ ማለት ነው ፤ ሥርወ ግሡም «አተበ» አመለከተ ፤ ባረከ የሚለው የግዕዝ ቃል ነው ። ምልክት ሁል ጊዜ አንዱን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያስችለው በመሆኑ ዓለም ይጠቀምበታል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በአራተኛው ምዕራፍ ስለ አብርሃም ሲናገር «ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ» ብሏል ። ወላጆችም መንታ ሲወልዱ የትኛው ቀድሞ እንደተገኘ ለማስታወስ ምልክት ያደርጋሉ ። ለምሳሌ በአራቱ ፋሬስና ዛራ ሲወለዱ አዋላጅዋ ቀድሞ በተወለደው አውራ ጣት ላይ ክር አሥራበት እንደነበረ ይነገራል ።

## የትመጣው በታሪክ መልክ

የኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ማተብ ማሠር ልማድ የመጣው ለረዥም ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችን ሞግዚት ሆና ከቆየችው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስ ቲያን ነው ። በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቴዎዶስዮስ ዘመን በሀገሩ የነበረው ዐላዊ ንጉሥ በመሆኑ የክርስትናን አስተማሪዎች እያሠረ ያስደበድብ ነበር ። ስለዚህም ቴዎዶስዮስ ካልሆነ ሰው ጋር ተጋፍጦ ከመቀሰፍና ሥራን ከማቋረጥ ዘወር ብሎ መዓቱን ማሳለፍ ይሻላል በማለት ሲሸሽ ፣ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ የሚባል ለክርስትና ትምህርት ቀናተኛ የሆነ ሐዋርያ በሽሽግ ያስተምር ነበር ። ይህንም የተቀደሰ ሥራውን ለማሰናከልና ለማቋረጥ የሚሹ አንዳንድ ቦዘን ተኞች በስብሰባው ላይ እየተገኙ ያስተማራቸውን ያስቱበት ያሻክሩበት ስለነበር የርሱ የሆኑትን ለይቶ ለማወቅ ሲል በአንገታቸው ላይ አድርገው ለምልክት ነት እንዲጠቀሙበት ማተብ አሠረላቸው ፤ ያሠረላቸውም ማተብ ሦስት ዓይ ነት ባንድ ላይ የተገመደ ሲሆን ጥቁር ፤ ቀይ ፤ ብጫ ነበር ። ይኸውም ጥቁሩ መከራ ለቀበላለሁ ፡ ቀዩ ደሜን አፈሳለሁ ፤ ብጫው ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ አደርጋለሁ የሚል እንደነበረ ይነገራል ። ያዕቆብ ዘእልበረዳኢም ያስተምር የነበረበት ዘመን አምስተኛው መቶ ዓመት እንደነበረ ይገመታል (ሃይማኖተ አበው ፡ ድርሳነ ያዕቆብ ። )



www.ethiopianorthodox.org

## በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው መልክ

ከግቴ ብርሃን ሰላማ በአራተኛው መቶ ዓመት ወደ ሀገራችን መጥቶ የክርስትና ትምህርት ፋናን ሲተክል ያመነ የተጠመቀውን ካላመነው ለመለየት ከግንባሩ ላይ በመብጣት መስቀልኛ ምልክት ያደርግ ነበር ይባላል ። ግን የመብጣቱና ደም የማፍሰሱ ዘዴ በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ በሙሉ ስለአልተደገፈ ከጊዜ በኋላ እንዲቀረ ይነገራል ። አሁንም ሳይቀር ሰሜናውያን ከግንባራቸው ላይ ምልክት የሚታይባቸው ከዚሁ ሲያያዝ መጥቶ ነው ይባላል ።

ምንም እንኳን መቼ እንደተጀመረ ከስንተኛውም መቶ ዓመት ጀምሮ እንደምትሠራበት በቂ መረጃ ባይገኝም ቤተ ክርስቲያናችን የማተብ ማሠርን ልማድ በደንብ ታከብራለች ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት መሠረት አንድ ሕፃን ወይም አንድ ሰው ሲጠመቅ ሦስት የተለያየ ቀለም ያላቸው ፈትሎች ከአንድ ላይ ተገምደው ለዚሁ የተወሰነው ጸሎት ተደርሶባቸው ለተጠማቂው ይታሠሩለታል ፤ ክሩም ነጭ ቀይና ሰማያዊ ሲሆን ፤ ነጩ ሐዲስ ሕግን/ ወንጌልን/ እጠብቃለሁ ፤ ቀዩ በክርስቶስ ፍጹም ድኅነት እንደማገኝ አምናለሁ ፤ ሰማያዊውም ሰማያዊ ሕግን በመጠበቅ ሰማያዊ ሕይወትን ተስፋ አደርጋለሁ ማለት እንደሆነ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያትታሉ ። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ምልክት በአንገቱ ላይ በማድረግ አባልነቱን ታጸናለታለች ።

## ከሕዝቡ ልማድ ጋር ያለው ግንኙነት

የማተብ ማሠር ሁኔታ ከሊቃውንቱ ይልቅ በሕዝቡ ዘንድ በጣም የጠበቀ ሆኖ ይታያል ። ከዚሁም የተነሣ በሕዝባዊ አነጋገር ዕገሌ ማተብ የለውም ሲባል ሃይማኖት የለውም በእምነቱ ያልጠበቀ ወላዋይ በተናገረው የማይቆም እግዚአብሔርን የማይፈራ ማለት ሲሆን ዕገሌ ማተብ ያለው ሰው ነው ሲባል ደግሞ ከማለ የማይከዳ የማይዋሽ የማይቀጥፍ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት የሚል የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ተደግፎ የሚራመድ ማለት ነው ። አሁንም በጊዜያችን በዚህ ሃሣብ የተመሠረተ ባሕላዊ ሙዚቃ/ ዘፈን/ « ባለማተቢቱ« በሚል መነሻ ይጀምራል ፤ የድርሰቱም ጠቅላላ ሃሣብ ወደተቀደሰው ጋብቻ ስትገቢ የሁሉታችንንም አንድነት ተረድተሺ ቀይ ስታይ ቀይ ፤ ጥቁር ስታይ ጥቁር ሳትሆኝ በሰላም ልጆችሽን የምታሳድጊው ኢትዮጵያዊት የተባረክሽ ነሽ በማለት በሃይማኖት ክልል ውስጥ ሁና ሲመቻች ብቻ ሳይሆን በመከራም ባለቤቷን አክብራ የምትኖረውን ቤት የሚ



ያሞግስ ነው ። ይህም ራሱ ባለማተብ ማለት በሕዝብ ዘንድ ምንም ያህል ግልጽ እንደሆነ ያስረዳል ።

## ጥቅሙና ጉዳቱ

ማተብ ማሠር በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ለብዙ ጊዜ ጸንቶ ለመኖር የቻለው ጥቅሙ የጐላ ሆኖ በመገኘቱ ነው ። ለአንድ ሀገር አንድ ሰንደቅ ዓላማ ለአንድ መሥሪያ ቤትም አንድ ዓይነት የጽሑፍ ምልክት ወይም አርማ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ላለ ሕዝብም አንድ ዓይነት ምልክት በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎችም በዚሁ ምልክት ሲጠቀሙ ቆይተዋል ፤ አሁንም በመጠቀም ላይ ይገኛሉ ። ይህ ምልክት በሀገራችን በሃይማኖት አንድነት የሌላቸው ሁሉ በአንድነት ሊፈጽሙት የማይገባቸውን ከመፈጸም እንዲድኑ ከማድረጉ በላይ አንድ መንገደኛ ሰው ሞቶ በተገኘ ጊዜ ክርስቲያንነቱ በዚሁ ምልክት አመልካችነት ተረጋግጦ አስፈላጊው ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎለት በዐፀደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀበር በማድረግ ሲያገለግል ቆይቷል ።

በጊዜያችን ግን ሃይማኖት በልብ ነው ምልክትም አያስፈልገውም በማለት በዚህ ምልክት የማይጠቀሙት እየበረከቱ ሄደዋል ። የሚሰጡትም ምክንያት ጽዳት ያጐላል የሚል ነው ፤ ጽዳት የማጉደሉ ሁኔታ ግን እንዳያያዙ ነው ፤ የ ሚፈለገው ምልክትነቱ ነው እንጂ አንዳንዶቹ እንደሚያደርጉት ያሥራ አምስት ክታብ ወይም ግሥንግሥ መሰብሰቢያ ማድረግ አይደለም ። ቤተ ክርስቲናችን ግን በሥነ ሥርዓቷ ብትፈጽመውና አስፈላጊነቱንም ብትገልጽ አንዱን ክርስቲያን ይህን ምልክት ሳታደርግ ቀረህ ብላ ከአባልነት አትለየውም አታወግዘውም ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ማተብ ማሠር ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ጥቅሙ በሊቃውንቱና በሕዝቡ ዘንድ ተጠንቶ ለብዙ ጊዜ ቢሠራበትም የተጀመረው ምናልባት በተሳቱ ቅዱሳን ጊዜ ይሆናል ተብሎ ከመገመቱ በቀር በዚህ ጊዜ ተጀመረ ዕገሌ አጸደቀው አስተማረው የሚል በቂ መረጃ ማግኘት አልተቻለም ። ያንዳንድ ሰዎች አስተያየት ደግሞ ምልክትነቱ ተደጋፊ ሆኖ ሳለ ደህና ቦታ ስለአላገኘ አገልግሎቱ አጭር ነው የሚል ነው ። ይህ አንድ ተደጋፊ አስተያየት ቢሆንም ነገሩን ችላ ለማለት ተተኪውን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ።

አእምሮ ማንደፍሮ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የዐርብና የረቡዕ ጾም ዝርዝር ሐተታ

## ጾመ ድኅነት

### ፩ኛ ጾመ ድኅነት ፡ የትመጣው

መቼም ጾም የሚጾመው ለንስሐ ወይም በኃጢአት ከሚመጣው ፍዳ ለመዳን ስለሆነ በመሠረቱ ጾምን ያመጣው ኃጢአት ነው ለማለት ይቻላል ። ሆኖም አሁን የተነሣነው ለምን በየሳምንቱ ዓርብና ረቡዕን ብቻ ለይተን እንደምንጾምና ይህም ጾም ለምን ጾመ ድኅነት ተብሎ እንደ ተሰየመ ለማወቅ ስለሆነ ሌላውን ሐተታ ለሌላ ጊዜ ትተን ወደዚሁ እንመለሳለን ።

እርግጥ ነው ያለአንዳች ምክንያት ከሰባቱ ዕለታት በተለይ ዓርብና ረቡዕን ብቻ ለመጾም አልተገደድንም እንዲያው ያለ ግብሩም ጾመ ድኅነት ብለን አልሰየምነውም ፤ ምክንያት አለው ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የዓርብና ረቡዕ ጾም ከጾመ ዮዲትና ከጾመ አስቴር የተመሠረተ ነው ፤ ጾመ ድኅነት የሚል ስያሜ የተሰጠውም በዮዲትና በአስቴር ጾም የእሥራኤል ሕዝብ ከጠላት ወረራ ሊድን በመቻሉ ነው እያሉ ያትታሉ ።

ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ግን ስለ አጽዋማት በሚናገርበት በአሥራ አምስተኛው አንቀጽ ለዓርብና ረቡዕ ጾም ምክንያት የሆነው የክርስቶስ ሕማምና ሞት መሆኑን ይገልጻል ። ስለሁኔታው በዝርዝር ሲያብራራም ክርስቶስ በአይሁድ ሸንጎ ረቡዕ ዕለት ይሙት በቃ ተፈርዶበት ዓርብ ስለተሰቀለ እነዚህ ዕለታት የጾም ቀን እንዲሆኑ መወሰኑንና የክርስቶስ ሕማምና ሞት ለዓለም ድኅነት ስለሆነም የእነዚህ ዕለታት ጾም ጾመ ድኅነት ተብሎ መሰየሙን ይናገራል ። አሳቡ የሚደገፍ ነው ። በማቴዎስ ወንጌል እንደ ተገለጸው አንድ ቀን ክርስቶስ ተማሪዎቹ ለምን እንደማይጾሙ ከፈሪሳውያን ዘንድ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ« የሙሽራው እድምተኞች ሙሽራው ከእነሱ ጋር እስካለ ድረስ ሊጾሙ አይችሉም ፤ ነገር ግን ሙሽራው ከእነሱ የሚለይበት ጊዜ ስለሚመጣ ያን ጊዜ ይጾማሉ» ሲል ተናግሮ ነበር ። በዚህ መሠረት ያ ቀን ደርሶ ክርስቶስ ተይዞ በተሰቀለ ጊዜ ተማሪዎች በእሱ ሞት ተደናግጠው ከእህልና ውሀ እንደ ታገዱ ይነገራል ። ፍትሐ ነገሥቱም ለዓርብና ረቡዕ ጾም መመሥረት ምክንያት አድርጎ ያተተው ይህኑ ስለሆነ ታሪኩን ለማስተባበል አንችልም ።



ቀኑ የተለየ ይሁን እንጅ ከክርስቶስ ልደትም በፊት ከሳምንት ሁለት ቀን መጾም በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር ፤ ቀኖቹም ማክሰኞና ሐሙስ ሲሆኑ ፤ በተለይ እነዚህን ዕለታት የሚጾሟቸው ሙሴ ሕግን ለመቀበል ወደ ደብረ ሲና ፩ኛ/ የወጣበት ፤ ፪ኛ/ የተመለሰበት ዕለታት በማለት ነበር ።

ያም ሆነ ይህ አሁን ይህን ሁሉ ታሪክ ለመዘርዘር የተገደድነው ምንጩ ያልተጣራ ውሀን ለመጠጣት ደስ እንደማያሰኝ እንዲሁ የት መጣው ያልታወቀ ይዞታም ለያገቡ ቅር ስለሚያሰኝ ምንጩን ለመረዳት ያህል እንጅ ፤ እኛ በአሁኑ ጊዜ ከሳምንት ሁለት ቀን ዓርብና ረቡዕን የምንጾመው ያለፈውን ታሪክ ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን እኛ ራሳችን ጾመ ድኅነት ስለሚያስፈልገን ነው ።

### ፪ኛ በቤተ ክርስቲያን ያለው ይዞታ

ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ለዓርብ ረቡዕ ጾም ያላት ይዞታ ተመሳሳይ እንጂ ከቀድሞው የተለየ አይደለም ፤ ቤተ ክርስቲያን እንደዱሮው አሁንም የዓርብ ረቡዕን ጾም ታዛለች ፤ ምክንያቱም ከሳምንት ሁለት ጊዜ መጾም ከሳምንት ሁለት ጊዜ ራስን ለመመርመርና ለመቈጣጠር ስለሚያስችል ነው ።

ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ዕለታት ሠርግ እንዳይሠረግ ወስናለች ፤ የነዚህ ዕለታት የነግሁን የጥዋቱን ቁርባን ወደ ሠርክ ታስተላልፈዋለች ። ጾም እንደ ጸሎት በግልም በማኅበርም መከናወን እንዳለበት ስለምታምንም የዓርብና ረቡዕን ጾምም እንዲሁ በምሥጢር ወይም በግል ሳይሆን በማኅበር እንዲጾም ትፈቅዳለች ። የማኅበር ጾምና ጸሎትም ብዙ ጊዜ ተፈትኖ እንደ ተረጋገጠው ለአንድ ሀገርና ሕዝብ መድኅን መሆኑ አሁንም ስለማያጠራጥር ጾመ ድኅነት ብላ የሰየመችውን የዓርብ ረቡዕን ጾም አሁንም በዚያው በስሙ ትጠራዋለች ።

### ፫ኛ በሕዝብ ዘንድ ያለው ይዞታ

ይህ ጾም በሕዝብ አንድ ከፍተኛ ግምት እንደ ነበረው ቢታወስም ባሁኑ ጊዜ ግን ከሚጠብቁት የማይጠብቁት ሰዎች ቍጥር እየበዛ መሔድ ጀምሯል ። ይልቁንም በከተማው ሕዝብ ዘንድ የጾም ፍቅር እየተቀነሰ ስለሔደ ሰለጠን ከሚሉት ወጣቶች ወገን ዓርብና ረቡዕ የሚባል ጾም መኖሩንም የሚያስታውሱ ሰዎች መጠነኞች ናቸው ።

ገጠሬው ሕዝብ ግን አሁንም ስለጾም ያለው አስተሳሰብ ስላልተለወጠ በሁሉም ዘንድ ስለዓርብና ረቡዕ ከጾሙ ጋር አብሮ የሚዘምት ልምድ አለው ።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም መንገድ መሔድ ፤ ልብስ ማጠብ ፤ መድኃኒት መቅመስ ፤ ለጤንነት አይበጅም እያሉ ያሚርታሉ ፡፡ ሥር ማሾችና ቅጠል በጣሾችም ዓርብና ረቡዕ ያልተቈረጠ መድኃኒት አይሰምርም እያሉ ያመካኛሉ ። ይልቁንም ቃልቾች ዓርብና ረቡዕን የዛር ማንገሻ ቀን አድርገውታል ። ተኙቶ የሰነበተው ቃልቻ ዓርብና ረቡዕን ጠብቆ ያብዳል ያጒራል ። ይህም ማስተዋል ለጐደለው ሕዝብ መጥፎ ጠንቅ ስለሆነ ሲጾም የዋለው ሰው እንደገና ማታ በየቃልቻው ቤት ተሰማርቶ ዛር ሲያቆላምጥ ስለሚያድር ታጥቦ ጭቃ ይሆናል ። ይህ በስሕተት የገባ ባዕድ አምልኮት ስለሆነ መሰረዝ አለበት ፤ ከዚህ በቀር ሁሉም የጾም አገልግሎት የገባው ሕዝብ በመሆኑ ስለጾም ራሱ ቢመክር እንጅ አይመከርም ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

ምግብ ለሰው ተፈጠረ እንጅ ሰው ለምግብ አልተፈጠረም ፤ የሰው ጠባይ እንደ ነጭ ልብስ አሁን ታጥቦ አሁን የሚያድፍ ነገር በመሆኑ በየጊዜው ንጽሕና ያስፈልገዋል ። እንዲህ ከሆነ ሰው ከሳምንት ሁለት ጊዜ ሰውነቱን ለመቈጣጠር ዓርብና ረቡዕን ቢጾም ቢያንሰው እንጅ አይበዛበትም ።

ቄስ ተሾመ ዘሪሁን ።



# የቅዳሜና የእሑድ አከባበር ዬት—መጣ

ሰው በተፈጥሮው በብርቱ የማሰብ የመንቀሳቀስ ፤ የንቅናቄና የመሥራት ኃይል ቢኖረውም ፤ በዚሁ አንፃር ደግሞ የመንፈስ ጸጥታና ዕረፍትን የመፈለግ ባሕርይ ( ጠባይ ) ይታይበታል ።

ይህም በብርቱ የማሰብና የሥራ ንቅናቄ ኃይሉና ዕረፍትን የመፈለግ ባሕርይ ተለክቶ ተመዝኖና ቀመጥኖ የቱን ያህል መሥራትና የቱን ያህል የዕረፍት ጊዜ ማግኘት እንደሚገባው በማጥናት በተለይ በክርስቲየናዊ ሕግና ሥርዓት የሚመሩና በቅዱስ መጽሐፍ ዕውነተኛነት የሚያምኑ ወገኖች ሁሉ አምስት ቀን ሠርተው ሁለት ቀን ማረፍ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ጽሙዳን ሆነው በመዝሙርና በማኅሌት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም በማመስገን መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማከናወንና በተጨማሪም ሕሙማንን ለመጠየቅ ችግረኞችን ለመርዳት እርስ በርስ ተገናኝቶ ችግሩንም ደስታውንም እኩል ለመካፈልና ፍጡር ከፈጣሪ ፤ የሚገናኝበትን በነ ሥራ ምግባር ለማሳየት የሚበቁትን ሥራ ያከናውኑባቸው ዘንድ ሁለት የዕረፍት ዕለታት ተመድበዋል ። እነዚህም ዕለታት ቀዳሚት ሰንበትና እሑድ ሰንበት ናቸው ። ሰንበት ማለትም « ዕረፍት » ማለት ነው ።

## የሰንበታቱ አከባበር ሁኔታ

ከክርስቶስ ልደት በፊት ፩፻፹ ዓመታት ቀደም ብሎ በተሠራው ሕገ ኦሪት ከእግዚአብሔር ከተሰጡት አሠርቱ ትእዛዛተ ኦሪት በ፬ኛው ክፍል « ትቀድሰውና ታከብረው ዘንድ የሰንበትን ቀን ( ሰባተኛዋን ዕለት ቀዳሚትን ) አስብ ተብሎ ስለ ተጻፈ ከዓርብ ምሽት ጀምሮ የተዘረጋ ሳይታጠፍ ፤ የታጠፈም ሳይዘረጋ ከባድ ሸክም ከማንሳት ሩቅ መንገድ ከመሔድ ተቆጥቦ ፤ ቅጠል ከመቁረጥ ፤ ዕንጨት ከመፍለጥ ተከልክሎ ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ የተለመደ ነበር ። ከክርስቶስ ልደትና ክትንሣኤውም ዕለት በኋላ ግን ብዙ አከራካሪ ምክንያቶች ተፈጥረዋል ። ከምክንያቶቹም አንደኛው ክፍል ዕረፍተ ሥጋ የተገኘባት ቀዳሚት ሰንበት ዕረፍተ ነፍስ ለተገኘባት እሑድ ሰንበት አምሳል መርገፍ ሆና የቆየች ጊዜያዊት ምሳሌ ስለሆነች እንደ አይሁድ ወግና ሥርዓት በመጠናቀቅ ማክበር አይገባም ። በቀዳሚት ምትክ ዕረፍተ ነፍስ የተገኘባት እሑድ ሰንበት መከበር አለበት የሚል ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም ሐዋርያት ስብሰባ (ሲኖዶስ)፣ አድርገው ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ማስረጃዎችን በማቅረብ ሁለቱም ሰንበታት ማለት ቀዳሚትና እሑድ እንዲከበሩና በነዚህ ዕለታት ክርስቲያኖች ሁሉ በቤተ እግዚአብሔር እየተሰበሰቡ የእግዚአብሔርን አንድነቱን ፤ ሦስትነቱን የሚናገሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ በጸሎት ተጸምደው በመዝሙርና በማኅሌት እግዚአብሔርን በማመስገን ሥጋ ወደሙን ተቀብለው በጠቅላላ ፍጡር ከፈጣሪው የ ሚገናኝበትን መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ማሳየት እንደሚገባቸው ወሰኑ ።

ከዚህም ሌላ በ፬ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተነሣው ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ዘመን ፫፻፳፭ ሊቃውንት በኒቅያ ባደረጉት ጉባኤ ላይ የዚሁ ጉዳይ ተነሥቶ በሐዋርያት ሲኖዶስ የተላለፈውን ውሳኔ ከመረመሩ በኋላ እንዳለ በማጽናት በተለይ የእሑድ ሰንበትን አከባበር ታላቅነቷንም ከቀዳሚት ሰንበት በበለጠ ሁኔታ አጋነው ጽፈዋል ። ፍትሐ ነገሥት ፲፱ኛውን አንቀጽ ተመልከት ።

## ፪ኛ በሀገራችን የሁለቱ ሰንበታት አከባበር

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሁለቱም ሰንበታት አከባበር በሲኖዶስና በፍትሐ ነገሥት የተሰጠውን ጠቅላላ ድንጋጌ ተቀብላዋለች ፤ ዳሩ ግን የቀዳሚት ሰንበት አከባበር ውሳኔውን የተከተለ አይመስልም ። በመላው ኢትዮጵያ ቀዳሚት በአንድ በኩል ከሰዓት በፊት ያለው ጊዜ የሥራ ሰዓት ነው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀዳሚት በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የገበያ ቀን ናት ። ምንም እንኳ በአንዳንድ አውራጃዎች በተለይም በጐጃምና በቤጌምድር ጠ/ግዛቶች አንዳንድ ምዕመናን የዓርብ ውሃ በመቅዳትና ሌሎችንም ጥንቃቄዎች በመጠበቅ ቀዳሚት ሰንበትን እንደ እሑድ ሰንበት የሚያከብሩ ቢሆንም በአብዛኛው ሕዝብ ያልተደገፈ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ብሔራዊ በዓል ሊመሆን አልበቃም ።

የእሑድ ሰንበት አከባበር ግን የሲኖዶሱንና የፍትሐ ነገሥቱን ድንጋጌ የተከተለ ነው ። በዕለተ እሑድ የመንግሥትና የግል ድርጅት መ/ቤቶች ንግድ ቤቶችና የሌሎችም ተግባራት ሰድ ክፍል በጠቅላላ ዝግ ሆነው ይውላሉ ። አብያተ ክርስቲያናት ሌሊት በካህናት ፤ ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ ደግሞ በሕዝበ ክርስቲያን (ምዕመናን) ተመልተው ያረፍዳሉ ።

ከሰዓት በኋላም ሐኪም ቤቶች (ሆስፒታሎች) ፤ እሥር ቤቶች ፤ ሕሙማንንና እሥረኞች ወገኖቻቸውን በሚጠይቁ ሕዝቦች ተመልተው ያመሻሉ ። ስለ እሑድ ሰንበት ክብር ታላቅነት ልዩ ልዩ ድርሳናት ተጽፈዋል ፤ በተለይም



የሊቁ የአትናቴዎስ ቅዳሴ በመላ የዕለተ እሑድ ሰንበትን ክብር በቃለ አጋኖ የሚገልጽ ነው ። የእሑድ ሰንበትን ታላቅነት ከሚገልጹት ዝክረ ነገሮች ዋና ዋናዎቹም ፩ኛ/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚች ዕለት ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን የሚገልጽ ሲሆን ፤ ፪ኛው ደግሞ ምንም እንኳ ዘመኑና ጊዜው ተወስኖ ባይታወቅም ክርስቶስ ይህን ዓለም ለማሳለፍ የሚመጣው በዚችው ዕለተ እሑድ መሆኑን የሚገልጽ እምነትና ተስፋ አለ ።

## ፫ኛ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት በዓል አከባበር

ሰባተኛውን ቀን (ቀዳሚትን) አክባሪ በሚል ስያሜ ከሚታወቀው የአድቬንቲስት ሚሲዮን ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቀዳሚት ሰንበት ዕረፍተ ነፍስ ለተገኘባት እሑድ ሰንበት ጊዜያዊ ምሳሌ ሆና የቆየች መሆንዋን በመግለጽ በርሰዋ ምትክ ክርስቲያኖች ሁሉ እሑድ ሰንበትን ብቻ እንዲያከብሩ ያውጃሉ ። በዚህችም ዕለት ምዕመናን በሙሉ በየአብያተ ክርስቲያናትና በየጸሎት ቤታቸው ታላቅ ስብሰባ በማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ቅዱስ ሥጋ ወደሙን በመቀበል በጸሎትና በምስጋና ፤ በመዝሙርና ይህንም በመሳሰለው ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ክርስቲያናዊ ሥርዓት ይፈጽማሉ ።

## ፬ኛ ማጠቃለያና የግል አስተያየት

በእርግጥ ሰንበት የዕረፍት ቀን ነው ቢባልም በሌሎች ዕለታት ከሚፈጸመው ያላነሰ ተግባር ሊከናወንበት የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል ፤ በተለይም በዘመናችን ወጣቱ ትውልድ በፊቱ የተደቀነበት የሞራል ውድቀት (የሥነ ምግባር ወይም የጠባይ መበላሸት) ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊና አስጊ የወረርሽኝ (ተላላፊ) በሽታ ስለሆነ በነዚህ ዕለታት በሲኖዶስና በፍትሐ ነገሥቱ እንደተመለከተው የሞራል ዘመቻ ማዘጋጀትና ወጣቱን ትውልድ ማስተማር በመልካም ሥነ ምግባር ማነፅ ሰንበታቱን የማያሽር ቅዱስ ተግባር ስለሆነ የመመካከሪያ ፤ የመወያያና የመረዳጃ ዕለታት ሊሆኑ ይችላሉ ።

መክብብ አጥናው ፤



www.ethiopianorthodox.org